# ጥያቄዎች ጠይቁ

## ጠቃሚ ምክሩን ይማሩ

1. **መፅሀፉ እንዲስባችሁ ጥያቄዎችን ጠይቁ:** የመፅሐፉን የሽፋን ገፅ ተመልከት/ች። ጥቂት ገፆችን ተመልከት/ች። ታሪኩ ውስጥ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ተነጋገሩ።
2. **መፅሀፉ ውስጥ ስለሚገኙ ቃላት ጥያቄዎች ጠይቁ:** ግራ የሚያጋባ ቃል ሲኖር፣ ምን አይነት ድምፅ እንዳለው ተነጋገሩ። የቃላቱን ፍቺ ተነጋገሩ።
3. **መፅሀፉ ውስጥ ስለሚፈጠሩ ነገሮች ጥያቄዎች ጠይቁ:** በምታነቡበት ጊዜ ቆም ብላችሁ ተነጋገሩ። መፅሀፉ ሲያልቅ ስለተፈጠረው ነገር ወይም ስለተማራችሁት ተነጋገሩ።
4. **መፅሀፉን እንደ ተራኪ ስለማንበብ ጥያቄዎች ጠይቁ፡** ማንበብንና ቃላትን በስርዓት እና አርፍተነገሮችን ስሜትን በሚገልጽ መልኩ ማንበብን ተለማመዱ።

### ይሄ ጠቃሚ ምክር ለምን አስፈለገ?

ስለመፅሀፍት መነጋገር ልጅዎ ብዙ ቃላትን እንዲማር/ድትማር እና ስለሚያነበው/ምታነበው እንዲያስብ/ቢ ለማገዝ ቀላሉ መንገድ ነው። በተጨማሪም እርስበርስ የበለጠ ትተዋወቃላችሁ!

## ልጅዎን ይጠይቁ

*ለትናንሽ ልጆች፡*

- ይህ መፅሀፍ ስለምን የሚሆን ይመስልሀል/ሻል? ከመፅሀፉ ውስጥ ይሄንን እንድታስብ/ቢ ያደረገህ/ሽ ምንድን ነው?
- ይህ ቃል ከባድ ነው። ረጋ እንበል። ምን ፊደላት ይታዩሀል/ሻል?
- በታሪኩ መጀመሪያ ምን ተፈጠረ? ከመፅሀፉ ውስጥ አሳየኝ/ዪኝ።

*ለትላልቅ ልጆች፡*

- ይሄንን መፅሀፍ በማንበብ ምን ልትማር/ሪ ትችላለህ/ያለሽ?
- ቀጥሎ ምን የሚፈጠር ይመስልሀል/ሻል? ለምን?
- በዚህ ቃል ውስጥ የየትኛዎቹ ፊደላት ህብረት ይታይሀል/ሻል?
- ይሄንን አንዴ ደግመን እናንብበው እና በተራኪ ድምጽ እናንብበው።

## አዝናኝ ልምምድ

ከጓደኞች እና ቤተሰብ ጋር የመፅሀፍ ክበብ አዘጋጁ--በአንድ ሰው ቤት ወይም ቤተመፅሀፍት። ምግብ ጨምሩበትና ግብዣ ይሆናል!

ሁሉንም ሰው አንድ (ወይም ከዛ በላይ) ሊያነቡት የሚፈልጉትን የህፃናት መፅሀፍ ይዘው እንዲመጡ ጋብዙ። ከአሁን በፊት አንብበው የወደዱት ወይም ሌላ መፅሀፍ ሊሆን ይችላል። ልጆችዎ ትናንሽ ከሆኑ የስዕል መፅሀፍትን ብቻ ተጠቀሙ። ቀጥሎም መፅሀፍት ተቀያየሩ።

በጥቂት ሳምንታት ውስጥ በድጋሚ ተገናኝታችሁ ስለመፅሀፍቱ ተነጋገሩ። የሚከተሉትን በመጠየቅ ውይይቱን ማስቀጠል ትችላላችሁ:

- ይሄ መፅሀፍ ስለ ምን ነበረ?
- የዚህ መፅሀፍ ምርጥ ክፍል ምንድን ነው? ለምን?
- ሌላ ምን መፅሀፍ ወይም ታሪክን አስታወሳችሁ?